01

أكاديمية إفريقيا
Africa Academy

አፍሪካ አካዳሚ ዲፕሎም የሽሪዐ ፕሮግራም

የትማሪ መመሪያ



የአንድ ዓመት የሽሪዓ ዲፕሎማ ፕሮግራም መግለጫ

ይህ ፕሮግራም በአንድ ዓመት ጊዜ ገደብ ውስጥ ተማሪዎችን በሽሪዓ እውቀት ላይ ያተኮረ ጥልቅ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የተነደፈ የዲፕሎማ መርሃ-ግብር ነው።

- **የምዝገባ ሒደት**፦ ትምህርቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ በቂ ዝግጅት እንዲደረግ፣ የተማሪዎች ምዝገባ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ይከናወናል። የምዝገባ ሂደትና ተያያዥ መረጃዎች በአካዳሚው ይፋዊ የሶሻል ሚዲያ ገጾች እና በአፍሪካ ቲቪ (Africa TV) አማካኝነት አስቀድሞ ለህዝብ ይፋ ይደረጋል።
- **የሰርዓተ-ትምህርት መዋቅር**፦ ይህ የዲፕሎማ ፕሮግራም በውስጡ ሁለት ሴሚስተሮችን ያካተተ ሲሆን፤ ተማሪዎች በእያንዳንዱ ሴሚስተር ስድስት (6)፣ በአጠቃላይ አሥራ ሁለት (12) መሰረታዊ የትምህርት ዓይነቶችን በጥልቀት ይከታተላሉ።
- **የምረቃ መስፈርት**፦ ተማሪዎች የሁለቱንም ሴሚስተሮች ማጠቃለያ ፈተናዎች በብቃት አጠናቀው ሲያልፉ፣ ከአካዳሚው እውቅና ያለው የፕሮግራሙ ማጠናቀቂያ ምስክር ወረቀት ይበረከትላቸዋል።

ፕሮግራሙን ልዩ የሚያደርጉት ነጥቦች

ነጻ መሆኑ

ኦንላይን ባሉበት መማር ይችላሉ

ጊዜ ገደቡ አንድ አመት ብቻ

የእድሜ ገደብ የለውም

የምሰክር ወረቀት

ፕሮግራሙ እለታዊ ትምህርቶች፣ጥያቄዎችና ፈተናዎችን ያካተተ ነው

የትምህርት አሰጣጥ ሰልት (BLOCK-BASED COURSE SYSTEM)

በዚህ የዲፕሎማ ፕሮግራም ውሰጥ የሚሰጡ ትምህርቶች በኮርሶች የተዋቀሩ ሲሆን፣ የትምህርት አሰጣጥ ሂደቱም አንዱ ኮርሰ ተጠናቆ ሌላው የሚቀጥልበት ተከታታይነት ያለው ሰልትን የተከተለ ነው።

በዚህም መሰረት፣ ተማሪዎች በአንድ ጊዜ ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች ደርበው ከመማር ይልቅ፣ የተመደበውን አንድ ኮርሰ ሙሉ በሙሉ አጠናቀው ፈተናውን ካለፉ በኋላ በቀጥታ ወደ ሚቀጥለው ኮርሰ ይሸጋገራሉ። ይህ አሰራር ተማሪዎች ትኩረታቸውን በአንድ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ብቻ በማድረግ ጥልቅ እና ውጤታማ እውቀት እንዲቀሰሙ ይረዳቸዋል።

የዲፕሎማ ፕሮግራም ጊዜ ገደብ

ዲፕሎማ የሽሪዓ ትምህርት ፕሮግራም በሁለት ሴሚስተር የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ የአንድ ሴሚስተር ጊዜ ገደብ በአጠቃላይ ፈተናና እረፍት ጭምር 6 ወር ነው።

የአንድ ኮርስ ጊዜ ገደብ

የአንድ ኮርስ ጊዜ ገደብ ፈተናና እረፍትን ጨምሮ 4 ሳምንት ነው። ከሳምንቱ ቀናቶች 6 ቀን የትምህርት ቀናቶች ሲሆን አንዱ ቀን እረፍት ነው።

በዲፕሎማ የሽሪዓ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ የትምህርት መከታተያ መንገዶች

ዌብሳይት

ይህ ዋናው የትምህርት መከታተያ ገፅ ሲሆን ተማሪው የአካዳሚው ዌብሳይት ላይ የሚከተሉትን መጎብኘት ይችላል፦

- የሚለቀቁ ትምህርቶች(በምሰል፣ በድምፅ እና በንባብ)
- ፈተናዎችን ማከናወን
- ውጤቶች እና የደረጃ መዝገብ መመልከት
- የዲፕሎማ ማጠናቀቂያ ሰርተፊኬት ማውረድ እና መመልከት

እነዚህን ተግባራት ለማከናወን ማንኛውም ተማሪ ግዴታ በአካዳሚው ዌብሳይት ላይ አካውንት ሊኖረው(ሊመዘገብ) ይገባል።

የቴሌግራም ቻናል

ሁለተኛው የትምህርት መከታተየ ሲሆን ተማሪው በሱ አማካኝነት የሚከተሉትን በፍጥነት መጎብኘት ይችላል፦

- ዕለታዊ ትምህርቶችን መከታተል።
- ትምህርት ነክ ማሰታወቂያዎች እና ማሰታወሻዎች መከታተል።

ለሁሉም ዙር ራሱን የቻለ የቴሌግራም ቻናል ያለ ቢሆንም ተማሪው በቴሌግራም ቻናል ላይ ፈተናን ማከናወን አይችልም።

የአንድ ኮርሰ ጊዜ ገደብ ፈተናና እረፍትን ጨምሮ 4 ሳምንት ነው። ከሳምንቱ ቀናቶች 6 ቀን የትምህርት ቀናቶች ሲሆን አንዱ ቀን እረፍት ነው።

የቲቪ ቻናል

ሶሰተኛው የትምህርት መከታተያ ሲሆን ተማሪው የሚከተሉትን ይከታተላል። በአፍሪካ ቲቪ አማካኝነት ተማሪው ኢንተርኔት ሳያሰፈልገው ዕለታዊ ትምህርቶችን መከታተል ይችላል።

የሚሰጡ የኮርሶች አይነት

- አቂዳ
- ተፍሲር
- ፍቅህ
- ተርቢያ
- የነቢዩ ሲራ
- ሐዲሰ

የአንድ ኮርሰ የትምህርት ብዛት ከ12 እሰከ 18 ገደማ ነው።


ትምህርቶቹ የሚሰጡበት መንገዶች

በአፍሪካ አካዳሚ ውሰጥ ትምህርቶች በተለያዩ መንገዶች ይሰጣሉ። ከነዚህ መካከል፦

- በጹሁፍ መልክ፡ ለያንዳንዱ ኮርሰ በPDF መልክ መጽሐፍ ተዘጋጅቶ ለየትምህርቱ ተከፋፍሏል።
- በቪዲዮ መልክ የሚቀርብ ሌክቸር፡ እሱም ለመጽሐፉ ማብራሪያ የተቀረጹ ቪዲዮዎች።
- በኦዲዮ መልክ፡ ለመጽሐፉ በኦዲዮ መልክ የተቀዱ የድምጽ ማብራሪያዎች ይገኛል።

የኮርሱ PDF፣ ቪዲዮ እና ኦዲዮ በአካዳሚው ዌብሳይት ላይ የሚገኝ ሲሆን የቴሌግራም ቻናል ላይም ይለቀቃል።


ሌክቸሩ ቆይታ በአማካይ 30 ደቂቃ ገደማ ይፈጃል። ሌክቸሩ በመርሃ ግብሩ መሰረት በአፍሪካ ቲቪ ይለቀቃል። በተጨማሪም ትምህርቶቹ የሚደገሙባቸው መርሃ ግብሮች ይኖራል።



ፈተናዎች


ሳምንታዊ ፈተናዎች:-

- ተማሪው በሳምንቱ መጨረሻ በዚያው ሳምንት ከተማረው ወሰጥ የመመዘኛ ጥያቄዎች ይፈተናል።
- እያንዳንዱ ኮርሰ እንደየ ይዘቱና ብዛቱ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሳምንታዊ ፈተናዎች ሊኖሩት ይችላል።
- እያንዳንዱ ሳምንታዊ ፈተና ከ10 የሚያዝ ሲሆን ይህ ውጤት በኮርሱ ድምር ላይ ይካተታል።
- ሳምንታዊ ፈተናው በየሳምንቱ ጁሙዐ ቀን ተከፍቶ እሁድ ማታ 1 ሰአት ይዘጋል። ተማሪው በዚህ ጊዜ ገደብ ውሰጥ በሚመቸው ሰአት ገብቶ መፈተን ይችላል።
- የፈተና ጊዜ ገደብ 30 ደቂቃ ሲሆን የሚጀመረውም ተማሪው ልክ ፈተናውን ከከፈተበት ሰአት አንሰቶ ነው።



ማጠቃለያ ፈተና

- ይህ ፈተና በየኮርሱ መጨረሻ የሚሰጥ የመመዘኛ ፈተና ሲሆን ተማሪውም ፈተናውን የመውሰድ ግዴታ አለበት።
- ማጠቃለያ ፈተናው ከ80 የሚያዝ ሲሆን በኮርሱ ድምር ውጤት ውስጥ ይካተታል።
- የኮርሱ ማጠቃለያ ፈተና የሚከፈተው ተማሪዎቹ ኮርሱን ተምረው ከጨረሱ በኋላ ሲሆን ፈተናው የሚቆየው ለ3 ቀናት (72 ሰዓታት)ነው።
- የፈተና ጊዜ ገደብ 3 ሰአት ሲሆን የሚጀመረውም ተማሪው ልክ ፈተናውን ከከፈተበት ጊዜ አንሰቶ ነው።



ማካካሻ ፈተና

- ይህ ፈተና በተለያየ ምክንያት ማጠቃለያ ፈተና ላመለጣቸው እና በኮርሱ ድምር ከ 50% በታች ላመጡ ተማሪዎች የሚሰጥ ነው::
- የማካካሻ ፈተናዎች ለሁሉም የትምህርት ዓይነቶች የሚዘጋጁት በሴሚስተሩ መጨረሻ ላይ ሲሆን ጊዜውም ሴሚስተሩ ካለቀ በኋላ በማስታወቂያ የሚገለጽ ይሆናል።
- እያንዳንዱ ፈተና ከ 80 ነጥብ የሚያዝ ይሆናል
- የማካሻ ፈተናዎች ለሁሉም የትምህርት ዓይነቶች በአንድ ጊዜ እና ለአሰር ተከታታይ ቀናት ክፍት የሚሆኑ ሲሆን፣ ተማሪው በዚህ ጊዜ ውስጥ በማንኛውም ሰዓት ፈተናውን መውሰድ ይችላል።
- የፈተናው ጊዜ፡ በአንዳንድ አገሮች የሚስተዋለውን የኢንተርኔት መቆራረጥ (መናጋት) ከግምት ውስጥ በማስገባት ክፍት የተደረገ ሲሆን፣ የፈተና ቀናት ሲያበቃ የሚዘጉ ይሆናል።



ውጤት አያያዝ

በአካዳሚው ውሰጥ የሚሰጡ ማናቸውም ኮርሶች የውጤት አሰጣጥ እና የተማሪዎች ዝውውር በሚከተለው መመሪያ መሰረት ይከናወናል፡

- **የማርክ ድምር አሰጣጥ፡-** የእያንዳንዱ ኮርሰ አጠቃላይ ድምር ውጤት ከ100 ነጥብ የሚሰላ ይሆናል።
- **የማለፊያ ነጥብ፡-** አንድ ተማሪ ለማለፍ በእያንዳንዱ ኮርሰ አጠቃላይ ድምር 50% እና ከዚያ በላይ ማምጣት ይኖርበታል።

ተማሪው ከአንድ ሴሚስተር ወደ ቀጣዩ ሴሚስተር ለመዘዋወር፣ በወሰዳቸው ሁሉም ኮርሶች ላይ የማለፊያ ውጤት ማሰመዝገብ ይኖርበታል። በአንዱም ኮርሰ ቢሆን ከ50% በታች ውጤት ካለው ወደ ቀጣዩ ሴሚስተር መሻገር አይችልም።



የውጤት መግለጫ ጊዜና የምረቃ መሰፈርት

- ተማሪው እያንዳንዱን ኮርሰ እንደጨረሰ ያመጣውን ግላዊ ድምር ውጤት ማየት ይችላል።
- የሴሚስተሩ አጠቃላይ ሙሉ ውጤት የሚለቀቀው፣ ተማሪው የሴሚስተሩን ሁሉንም ኮርሶች ተፈትኖ ካጠናቀቀ በኋላ ብቻ ይሆናል።
- ተማሪው የአካዳሚው ተመራቂ ለመሆን በሁለቱም ሴሚስተሮች የተሰጡትን ትምህርቶች (ኮርሶች) በሙሉ በሰኬት ማጠናቀቅ (ማለፍ) ይኖርበታል።



የዲፕሎማ ሰርተፊኬት

- ተማሪው እያንዳንዱን ኮርሰ እንደጨረሰ ያመጣውን ግላዊ ድምር ውጤት ማየት ይችላል።
- የሴሚስተሩ አጠቃላይ ሙሉ ውጤት የሚለቀቀው፣ ተማሪው የሴሚስተሩን ሁሉንም ኮርሶች ተፈትኖ ካጠናቀቀ በኋላ ብቻ ይሆናል።
- ተማሪው የአካዳሚው ተመራቂ ለመሆን በሁለቱም ሴሚስተሮች የተሰጡትን ትምህርቶች (ኮርሶች) በሙሉ በሰኬት ማጠናቀቅ (ማለፍ) ይኖርበታል።



የዲፕሎማ ሰርተፊኬት

- የዲፕሎማ ሰርተፊኬት ለተማሪው የሚሰጠው፣ በሁለቱም ሴሚስተሮች በሙሉ በሰኬት አጠናቆ ሲያልፍ ብቻ ነው።
- ይህ የዲፕሎማ ሰርተፊኬት በመንግሰት መሥሪያ ቤቶች ዘንድ ይፋዊ ዕውቅና የሌለው መሆኑን ከወዲሁ እንገልጻለን።ሆኖም ግን፣ ተማሪዎች በግል ዘርፍ በሚወጡ የሥራ ማሰታወቂያዎች ላይ ለማመልከት፣ የሙያ ብቃታቸውን ለማሳደግ እና በግል ድርጅቶች ውሰጥ ተቀጥረው ለመሥራት በከፍተኛ ደረጃ ይጠቅማቸዋል።



የቴክኒክ ድጋፍ እና ግንኙነት (TECHNICAL SUPPORT

- **የቴክኒክ ድጋፍ፦** ተማሪዎች ከትምህርቱ ሂደት ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ጥያቄዎች ለመጠየቅ ወይም የቴክኒክ ችግሮች ሲያጋጥሟቸው ፈጣን እገዛ ለማግኘት የቴክኒክ ድጋፍ ክፍሉን ማነጋገር ይችላሉ።
- ከተማሪዎች ጉዳይ አስተባባሪዎች ጋር ለመገናኘት እና የተለያዩ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ለመጨረስ ከታች ያለውን የቴሌግራም አድራሻ መጠቀም ይቻላል፦

ቴሌግራም፦ @ethio_africaacadem